## ብፁዕ አቡነ ብርሃነየሱስ ሊቀ ጳጳሳት ዘካቶሊካውያን የ2004 ዓ.ም የዘመን መለወጫ በዓልን በማስመልከት ለምዕመናን ያስተላለፉት መልዕክት፡፡

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

"ኢየሱስም እንዲህ አላቸው የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምን ከቶ አይጠማም፡፡" (ዮሐ 6.35)

የተወደዳችሁ ምዕመናን
ክቡራን የቤተክርስቲያን አገልጋዮች፣
በሀገር ውስጥና ከአገር ውጪ ያላችሁ ኢትዮጵያዊያን ወገኖች፣
በጎ ፍቃድ ያላችሁ ሰዎች በሙሉ፣

ከሁሉ በማስቀደም ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝቦችና ለካቶሊካውያን ምዕመናን በሙሉ እንኳን ከዘመነ ሉቃስ ወደ ዘመነ ዮሐንስ በሰላም አሸጋገራችሁ፤ ልዑል እግዚአብሔር እንኳን ለ2004 ዓ.ም በሰላምና በጤና አደረሳችሁ በማለት ልባዊ የሆነ መልካም ምኞቴን እገልፅላችኋለሁ፡፡

እግዚአብሔር ሆይ!
ከዘመናት እስከ ዘመናት መጠጊያ ሆነኸናል፤ መዝሙር 89፡1
እኛ የሰው ልጆች የሆንን በሙሉ ይህን የዘመን መለወጫ በዓል ስናከብር በይበልጥ እግዚአብሔር ፈጣሪያችንን የምናመሰግንበት መሆኑን በመገንዘብ ነው፡፡ እንዲሁም በእሱ መጠጊያነት ያለፈውን ዓመት በሰላም አስፈጽሞን እነሆ አዲሱን ዓመት ስንቀበል ለእርሱ በጎነትና ቸርነት ምስጋና በማቅረብ ሊሆን ስለሚገባ ነው፡፡

«ነፍሴ ሆይ! እግዚአብሔርን አመስግኚ፤ ቸርነቱንም አትርሺ» ይላል ዳዊት በመዝ.103.2

ፈጣሪያችን አዲስ ዓመትን በተለያዩ ወቅቶች ከፋፍሎ ይሰጠናል፣ ይህም ለኛ ለሰዎች ጥቅም ይውል ዘንድ በማሰብ ነው፡፡ የአዲስ ዓመት መምጣት አዲስ ሕይወት የሚያመጣልን የሚያድሰንና እንደገና ሙሉ ሰዎች የሚያደርገን ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ አዲስ ዓመት የተጣሉ ካሉ በዕርቅና በይቅርታ በመታደስ የእግዚአብሔርን ፍቃድ በመፈፀም ለሕይወታቸው ብርታትና ለእምነታቸው ዕድገት የሚበጅ መንፈሳዊ ዕድገት ላይ ለመድረስ የሚያበቃቸውን መልካም ስራ እንዲሠሩ አሳስባለው፡፡ አምላካዊ ቃልን

ሁልጊዜ ማስተዋል ይጠቅመናል፤ ለዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ «ክፉውን ነገር በመልካም ነገር አሸንፍ እንጂ በክፉ ነገር አትሸነፍ» ይላል ሮሜ፤12፡21።

ዘመናትን የሚሰጥና የሚቆጣጠር እግዚአብሔር ነው፤ ስለሆነም እግዚአብሔር የሚነግረንንና የሚፈልግብንን መስማትና ማድረግ ግዴታ አለብን።

አዲሱ ዓመት በሁላችንም ዘንድ ፍሬ ያለው ሊሆን ይገባል። ይህውም ለምድራዊ ኑሮአችን የምናጠፋውን ጊዜና የምናሳየውን ጥረት ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ዘለዓለማዊነት ልናውለውም ይገባል። ምክንያቱም ሁሉም የሚሆነው በእግዚአብሔር በመሆኑ በአዲሱ ዓመት አምላክ ይቀርበናል ይባርከናል የእያንዳንዳችንም ወዳጅ መሆን ይፈልጋል።

በአዲሱ ዓመት እያንዳንዳችን የየራሳችን ዕቅድና ሥራ ይኖረናል። በመሆኑም ዕቅዳችንንና ሥራችንን ፈጽመን ልንገኝ ይገባል። ለምሳሌ ባሳለፍነው ዓመት ከአቀድናቸው ነገሮች በከፊል የተከናወኑና ያልተከናወኑ ታቅደውም ያልተሞከሩ ነገሮች ይኖራሉ። ስለሆነም ማንኛውም ሰው እግዚአብሔር በሰጠው ጊዜ ያቀደውን ነገር መፈፀም ይኖርበታል እንጂ ማስቀረት የለበትም። ጊዜ ወደ ኋላ ሊመለስ አይችልም። በሕይወታችን ዘመን ሁልጊዜ እግዚአብሔር አለ፤ ዘወትር የምንኖረው በእርሱ ፊት ስለሆነ ጊዜ አለን ብለን የምንተወው ነገር መኖር የለበትም። በጊዜያችን ማድረግ የሚገባንን እናድርግ። ሕይወታችን ሁልጊዜ በጥሩ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር የተመሠረተ መሆን ይገባዋል። ይህም ጥሩ ክርስቲያናዊ አካሄድ ያስከትላል፤ እርሱም ከፉ በማድረግ ሳይሆን መልካም ነገር በማድረግ መመስከር ነው።

በአሁኑ ጊዜ ለትምህርትና ለልማት ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠበት ጊዜ ነው። እነዚህም ለሰው ልጆች እድገት ወሳኝ ነገሮች ናቸው። ዘወትር እየለመንን የምንኖር ሳንሆን አውቀንና ሠርተን እራሳችንን እና አገራችንን የበለጠ ማሳደግ ይኖርብናል። ስለዚህ የጀመርነው የአምስት አመቱ የእድገትና የመሠረታዊ ለውጥ ዕቅድ ያስከተለው የልማት ሥራ ተነሳሽነታችን አገራችንን ከፍተኛ እድገትና ክብር የሚያጎናፅፋት ይሆናል ብለን እንጠብቃለን።

የአዲሱ ዘመን መባቻ የሆነው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በኢትዮጵያውያን ተጀምሮ በኢትዮጵያን እንዲፈፀም ሁላችንም ባለው ትብብር በመቀጠል ለአገራችን ዕድገት ታላቅ ራዕይ የሆነው የሕዳሴው ግድብ ግቡን እንዲመታ በጸሎትና በሥራ እንድንተባበር አደራ እላለሁ።

በአሁኑ ጊዜ በአንዳንድ የሀገራችን ከፍሎች በድርቅ ምክንየት የምግብ እጥረት የደረሰባቸውን ወገኖች ከመንግሥትና ከበጐ አድራጐት ድርጅቶች ጋር በመሆን ሁላችንም እንድንረዳቸውና በሚቀየሰው የመልሶ ማቋቋም ሂደት እንድንሳተፍ አደራ እላለሁ።

ዛሬም በዘመናችን ገና ፈውስ ያልገተኘለት የኤች አይቪ ኤድስ በሽታ በመኖሩ፣ የህብረተሰባችን ግንዛቤም ከፍ ያለ ቢሆንም፣ ሁላችንም እራሳችንና ቤተሰባችንን ከዚህ በሽታ በመጠበቅ ጤናማ ዜጋ እንዲኖረን አሁንም ግንዛቤን የማስጨበጥ ትምህርቱና ቅስቀሳውን በየአቢያተ ክርስቲያናት፣ በሐዋርያዊ በማህበራዊና በልማት ስራዎቻችን ቦታና ዕቅዶቻችን ውስጥ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ አደራ እላለሁ።

መስከረም ሲጠባ ብርሃን ይፈነጥቃል፣አበቦች ያብባሉ፣ልጆች ይዘምራሉ፡፡ የአዲስ ተስፋ ጊዜ ነው፡፡ስለዚህ ሕፃናት፣ልጆችና ተማሪዎች በደስታ ትምህርታቸውን ለመቀጠል ወደ ት/ቤት ሲመለሱ በሥነ ምግባር ተኮትኩተው እንዲያድጉና ያገራቸው ብቁ ዜጎች እንዲሆኑ ወላጆች፣ መምህራንና ህብረተሰቡ ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለባቸው ማስገንዘብ እወዳለሁ፡፡ ሥነ ምግባር ያለው ዜጋ ፈሪሃ እግዚአብሔር ስለሚኖረውና ሕሊናውም ስለሚገዛው ከወንጀል፣ከሙስናና ከኢሰባአዊ ድርጊቶች እራሱንና ሌሎችን ይጠብቃል፡፡

ይህን በዓል ስናከብር ድሆችንና አቅመ ደካሞችን በተለያየ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ሕፃናትና ያለጡዋሪ ለቀሩት ቤተሰቦች በማሰብ አቅማችን የሚፈቅደውን በማድረግ በዓሉ የደስታና የፍቅር እንዲሆንላቸው እንድናደርግ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ፡፡

በመጨረሻም በአደረባችሁ ሕመም ምክንያት በሆስፒታሎችና በየቤቱ በሕመም ላይ የምትገኙ ሁሉ የምሕረት አባት ምሕረቱን ያውርድላችሁ፣ በከባድ ሀዘን ውስጥም ያላችሁትን እግዚአብሔር መጽናናትን ይስጣችሁ፣ በየማረሚያ ቤቶችም ሆናችሁ ይህን ክብረ በዓል የምታከብሩትንም እግዚአብሔር በምህረቱ ይፍታችሁ፣ በሥራና በተለያዩ ምክንያቶች ከቤተሰቦቻችሁ ርቃችሁ ለምትገኙ፣ በየጠረፉና የአገራችንን ድንበሮች በመጠበቅ ላይ ለምትገኙ ሁሉ እንዲሁም በውጭ ለምትኖሩ ኢትዮጵያዊንና ኢትዮጵያዊያት በሙሉ መልካም አዲስ አመት እንዲሆንላችሁ መልካም ምኞቴ ነው፡

አዲሱ ዓመት ዘመነ ዮሐንስ  የሰላም የጤና፣የፍቅር፣የበረከት፣የብልጽና የደስታ ዘመን ይሁንልን፡፡ አሜን!

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!!!